# የዴሞክራሲን ሥርአት ለማስፈን የፖለቲካ ልሂቃን ቁርጠኝነትና የህዝብ ግፊት አማራጭ የላቸውም

ከድልበቶ ደጎዬ ዋቆ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ትግራይ ኦንላይን ነሐሴ 05/2008

"የፓለቲካ ስልጣንን በአመፅ ከነጠቅህ በአመፅ ትገዛለህ፣ ልትወገድ የሚቻለውም በአመፅ ብቻ ነው።" (ፒክ ቦታ፣ የቀድሞው የአፓርታይድ ደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ታይም፣ ሰኔ 30/1986)።

ባጭሩ ለመግለጽ፣ ዴሞክራሲ በህዝብ ፈቃድ ላይ የሚመሰረት፣ ህዝቡ ሠላማዊና ነፃ በሆነ የድምፅ አሰጣጥ ሥርአት በየተወሰኑ ጊዜያት በሚመርጣቸው ተወካዮች እና በራሱ ህዝበውሳኔ በተደነገገው ማህበራዊ ውል (social contract) ወይም ህገመንግስት መሠረት የሚተዳደርበት አስተዳደር ማለት ነው። የመንግስት ባለሥልጣናትን የሚሾመውና የሚሽረው ህዝቡ ነው፣ የህዝቡን ፈቃድና ፍላጐት የሚፃረር አንዳችም ቡድን ወይም ፓርቲ ተቀባይነት አይኖረውም፣ ሊኖርም አይገባም። የባለስልጣናቱ ተጠያቂነት ለመረጣቸውና ለሾማቸው ህዝብ ነው። የሕግ የበላይነትና ነጻነት የሰፈነበት ሥርአት ነው ዴሞክራሲ። የቀድሞ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን እንዳስቀመጡት፣ "ዴሞክራሲ የህዝብ፣ ለህዝብ፣ በህዝብ የሆነ መንግሥት " ነው።

አያሌ የምእራብ አገሮች የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች እንደሚያቀነቅኑት፣ 1) አያሌ ብሔረሰቦች ባሉበት እና ፅኑ አንድነት በሌለበት አገር ሊበራል ዴሞክራሲን ለማስፈን አዳጋች እንደሆነ ነው(ስትዋርት ሚል፣ ፍራንሲስ ፉኩያማ)።2) በቂ የኢኮኖሚ አቅም የሌለው፣ ዘመናዊ ትምህርት የቀሰመና የሚመርጠውን በሚገባ ለመረዳትና ለመወሰን አቅም የሌለው ደሃ ህዝብ ለዴሞክራሲያዊ ሥርአት ደንታ አይኖረውም የሚሉ ምእራባውያን ደግሞ አሉ (ሊፕሴት)። 3) የዴሞክራሲ እሴቶች የምእራባውያን እሴቶች ስለሆኑ ሌሎች ህብረተሰቦች በቀላሉ ሊማሩዋቸው አይችሉም የሚሉም አሉ(ቤርገር)። 4) በርካታ ብሔረሰቦችና ቋንቋዎች ቢኖሩም እንደህንድ የመሳሰሉት አገሮች በብሔር ማንነት ላይ ሳይሆን በዜግነት መብትና በህንዳዊነት የጋራ መታወቂያና ብሔራዊ መለያ ላይ የተመሰረተ እሴት በማስቀደምና ክልላዊ ፌዴሬሽን (ethno-regional federation) በመዘርጋት እንዲሁም የአገሪቱ አንድነት የማይሸራረፍና የማይደፈር፣ በሕገመንግሥቱ ውስጥ የመገንጠል መብት በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል አድርጎ በመደንገግ ሊበራል ዴሞክራሲን ለማስፈን ችሏል ብለው የሚከራከሩ ምሁራን ይገኛሉ(ማኖር 1996)።5) የፖለቲካ አመራር ቁርጠኝነትና የኢኮኖሚ ልማት ካለ በማንኛውም አገር የዴሞክራሲ ሥርአት ለማስፈን ይቻላል የሚሉ ታዋቂ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር አሉ(ሳሙኤል ሃንትንግተን)። 6) አያሌ ብሔረሰቦች ፣ ቋንቋዎችና ባህሎች ባሉበት አገር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፈን የሚቻለው ሁሉንም ብሔረሰቦች የሚያሳትፍ ሰፊ መሠረተ ያለው የጥምረት መንግሥት (coalition) በማደራጀት እንደሆነ አርተር ሊዊስ የተባሉ ምሁር ያስረዳሉ። 7) በመጨረሻም የሩቅ ምስራቅ እስያ አገሮች የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ፣ ደሃ አገሮች ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስገኘትና የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ፣ የማህበረሰቡን መስተጋብር በትምህርት ጭምር እምርታ እንዲያሳይ በማስቻል፣ የገጠር ሕይወት በወሳኝነት ወደከተሜነት በመለወጥ እና እንዱስትሪን በማሳደግ ወደሊበራል ዴሞክራሲ ለመሸጋገር ይቻላል በማለት ይከራከራሉ (ኬኒቺ)። ይህ ሁሉ አከራካሪ አስተሳሰብ እንዳለ ቢሆንም፣ ሁሉም የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን እንደሚስማሙበት የፖለቲካ ስልጣን ቁንጮ ላይ የወጡ ልሂቃን ዴሞክራሲን ለማስፈን የማያወላውል ቁርጠኝነት ካላቸው ዴሞክራሲ በአንድ አገር ውስጥ ሊያብብና ሊጎለብት እንደሚችል እንዲሁም የዴሞክራሲ እሴት በትምህርት የምናገኘው እሴት እንጂ በውርስ የሚተላለፍ እሴት አለመሆኑን ነው፣ ከውስጥ የሚለመልምና የሚያድግ ማህበራዊ እሴት እንጂ እንደሸቀጥ ከውጭ የምናስገባው አይደለም። ስለዚህም በትምህርት የምናገኘውን የዴሞክራሲ እሴት ወደተግባር ለመተርጎም ፍላጎትና ቁርጠኝነት ካለ ከጊዜ በሁዋላ እንደማንኛውም ዴሞክራሲያዊ አገር ይህንን እሴት በመንግሥት ቅርፅነትም ሆነ በኑሮ/በሕይወት ዘይቤነት ተግባራዊ ለማድረግ እንደምንችል ነው። ይህንንም እውን ለማድረግ ረዥም በጣም ረዥም ጊዜና ትእግሥት እንደሚያስፈልግ ሁሉም ምሁራን በአፅንኦት ያሳስባሉ።

ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነው ፣ የሪፖርተር ጋዜጣ "ህዝብ ዴሞክራሲ እንዲሰፍንለት እስከመቼ ይጠብቅ?" በሚል ርዕሰ አንቀፅ (ሐምሌ 29/2007) ስር ያቀረበው ትችት እና አሁን በቅርቡ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት በሐገር ውስጥና ከሐገር ውጭ የሚኖሩ በርካታ አትዮጵያውያን በኢትዮጵያ አለ የሚሉትን የፕሬስ ነፃነት መጣስና የጋዜጠኞች/የብሎገሮቸ መታሰር፣ የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ፣የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አለመከበር፣ የሕግ የበላይነት አለመኖር፣ ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋማት አለመዘርጋት እና የመሳሰሉትን ፓለቲካዊ ችግሮች በተመለከተ ፕሬዝዳንቱ በገዢው ፓርቲና መንግሥት ላይ ተፅእኖ እንዲያደርጉ በየመድረኩ ሲያነሱ የነበረው ማሳሰቢያና ውትወታ እንዲሁም የመሪዎቻችን የተለሳለሰ የመማፀን ኣይነት አቋም ነው፣ ከኢፌዴሪ መንግሥት ባለሥልጣኖች ሳይሆን ከአሜሪካ ጥገኛ ግዛት("banana republic") መሪዎች የሚጠበቅ የማጎብደድ ዝንባሌ ነው በቴሌቪዥን የታዘብነው፣ ተጠያቂነታቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ ሣይሆን ለአሜሪካን ፕሬዚዳንት ይመስል።

በኔ እምነትና ያለፈው የአለም ታሪክ እንደሚያረጋግጠው የዚህ አይነቱ የውጭ ጫና ዴሞክራሲን እንዲሁም ልማትን አያስገኝልንም፣ፋይዳውም እጅግ ዝቅተኛ ከመሆን አያልፍም።እንዲያውም የከፉ መዘዞችን ይዘው ከተፍ እንደሚሉ የአለም ታሪክ ያረጋግጣል ። ዴሞክራሲን ለመትከልም ሆነ ለሌሎች ችግሮቻችን ወሳኝ መፍትሔ የሚገኘው ከራሳችን በራሳችን ነው፣ በራሳችን መራራ ትግልና አርቆ አስተዋይነት ነው ድል የምንቀዳጀው። አዎን በራሳችን ተጋድሎና መስዋእትነት! ሌላ አቋራጭ መንገድና መፍትሄ የለውም በፍፁም። በዴሞክራሲ ሽፋን የምእራቡ አለም በኢራቅ፣ በአፍጋኒስታን፣ በሊቢያ፣ በሶሪያ፣ በቀድሞዋ ኢራን ወዘተ ካደረሱዋቸው የማያባሩ የእርስ በእርስ ጦርነቶችና ውድመቶች እውነታ ትምህርት ቀስመን ተገቢውን ጥንቃቄ ካለደረግን በስተቀር ውጤቱ አስከፊ እንደሚሆን ለመገመት አስቸጋሪ አይሆንም ። ሌላውን ትተን ለዘመናት የምንኮራበትን የሀገር ነፃነት፣ ሉአላዊነት እና ብሔራዊ ኩራት ለውጭ መሪዎችና አገሮች አሳልፈን እንድንሰጥ የሚለምኑ ዜጎች ይኖራሉ ብዬ አልገምትም።

ሁላችንም መገንዘብ ያለብን፣ ከግለሰብ ችግሮች አንስቶ በማናቸውም ደረጃ የሚያጋጥሙንን የዴሞክራሲና የልማት ችግሮችና ፈተናዎች ለማሸነፍ የምንችለው በራሳችን ጥረት፣ጥሪት፣ ዘዴና አቅም ነው፣ ምንም እንኳዋ እውቀትና የሌሎች ገንቢ እገዛ ከተገኙ የሚጠቅሙን ቢሆንም። ዛሬ የምናካሂደው መራራ ትግል በአንድ ወገን ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት በማምጣት ሕዝባችንን ከከፋ ድህነት ማውጣትና ብቃት/አቅም ያለው ዜጋ እንዲፈጠር ማገዝ ሲሆን በሌላ ወገን ደግሞ እውነተኛ ዴሞክራሲን በገዥው ፓርቲ የበላይነት ላይ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህዝብ ፈቃድና የበላይነት ላይ በማስፈን የዜጎችን ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን በሚገባ መጠበቅ፣ ለነዚህም መከበር ዋስትና የሚሆኑ ተቋአሞችን መዘርጋት ሲሆኑ ደጋግመን በየአጋጣሚው እንደምንናገረው ሁለቱም የትግል ፈርጆች የማይነጣጠሉ የህልውናችን ምሰሶዎች ናቸው ።አንዱን አስቀድሞ ሌላውን በይደር ለማቆየት መሞከር አደገኛ ውጤት ያስከትላል፣ ዴሞክራሲና ልማት ሊነጣጠሉ አይችሉም። ለዚህም ነው እኮ ልማታዊ ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት ነን (democratic-developmental state) ብለን ያወጅነው።

በተጨማሪ፣ ለእኛ በአፋኝ የአገዛዝ ስርኣቶች ለበርካታ ዘመናት ለተሰቃየንና ላሳለፍን ኢትዮጵያውያን ልክ እንደ1960ዎቹ ኮሪያ፣ ታይዋን እና ሲንጋፖር እኛም "ማንኛውንም ዋጋ ከፍለን የኢኮኖሚ ልማታችንን ማፋጠን አለብን" ("economic growth at any cost") የሚለው የመንግሥታችን መፈክር ከሁሉም በላይ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችንና የህግ የበላይነትን እንዲሁም የግለሰብና የማህበረሰብ ነፃነቶችን የሚደፈጥጥ የልማት አማራጭ ከሆነ በአሁኑ ዘመን ተቀባይነት አይኖረውም። በዚህ መንገድ የምናገኘው ልማት ምን የሚሉት ልማት እንደሆነ አይገባኝም፣ ልማት እኮ ከሰው ልጅ ልማት ውጭ ሊታሰብ አይችልም፣ ሊሆንም አይገባውም። ማናቸውንም ዋጋ ለዛሬውና ለነገው የልማት ትግሎችና ተስፋዎች የዛሬው ትውልድ የእውቀት፣ የሃብትና የጉልበት መስዋእትነት ከሚከፍል በስተቀር ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ጭምር እንዲሰዋ መጠየቅ ተቀባይነት የሌለው ጭፍን ፍርድ ነው። ዘላቂ ልማት ማለት (sustainable development) እኮ የዛሬውን ዜጎች መሰረታዊ ፍላጎቶች (ምግብ፣ መጠለያ፣ልብስ፣ህክምና፣ የስራ እድልና ወርሃዊ ገቢ፣ ነፃነት) እና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ፓለቲካዊና ማህበራዊ ፍላጐቶች በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ አብዛኛው ህዝብ ከፍርሃትና ከጭቆና ነፃ ወጥቶ በደስታና በሰላም እንዲኖር ማብቃት አልፎ ተርፎም መጪው ትውልድ ተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ እንዲኖር የሚያስችለው ሃብትና የሀብት ምንጭ መኖሩን ማረጋገጥ ነው። የዛሬውን ትውልድ ለመጪው ትውልድ ስንል መቅጣት አይደለም።

በእርግጥ፣ለዘመናት ከተንሰራፋው የድህነት አረንቋዋ ለመላቀቅ የመላውን ሕዝባችንን አመኔታና ድጋፍ ያገኘ፣ በነፃ የምርጫ ሥነሥርዓት በህዝቡ የተመረጠ፣ የመጠቀ የእውቀት ብቃት፣ የጠራ አይዲኦሎጂ ያለው፣ ትክክለኛ የኢኮኖሚክ ፓሊሲና የልማት ስትራተጂ የነደፈ፣ ከሙስና የፀዳ፣ አዳዲስ ሐሳቦችን ለማፍለቅ የሚችልና ትራንስፎርመሽናል የሆነ (innovative and transformational) ጠንካራ የመንግሥት አመራር እና ከገዢው ፓርቲ ወገንተኝነት ነፃ የሆነና የትምህርትም ሆነ የልምድ ከፍተኛ ብቃት ያለው የሲቪል ሰርቪስ እንዲኖር የግድ ነው፣ በተጨማሪ ግርማ ሞገስ (charismatic)፣ ቴክኖክራቲክ ብቃትና ራእይ ያለዉ መሪ። ይህ ማለት ግን አምባገናዊ መንግሥት እንዲኖረን ያስፈልጋል ማለት አይደለም፣ የአገሪቱን ሕገመንግሥታዊ ስርዓት የሚያከብር ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ አገዛዝ እንጂ።

እንግዲህ በወረዳም ሆነ በዞን፣ በክልልም ሆነ በፌደራል እና በሀገር ደረጃ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን እንዲሁም የህግ የበላይነትንና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአትን ለመገንባት የምንችለው፣ ሕገመንግሥታዊ ስርዓትን ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር የምንችለው ራሳችን በራሳችን ተጋድሎና ብርቱ ጥረት ብቻ ነው ። ከሁሉም በላይ በ1994 ያፀደቅነውን ህገመንግስት በተለይ የገዥው ፓርቲና መንግስት ባለሥልጣኖች ለማክበርና ለማስከበር ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ቁርጠኝነት የሚያሳዩበት ጊዜ አሁን ነው። ሲያመቸን የኢፌዴሪ መንግሥት የተመሰረተበትን ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት፣ ሳያመቸን ደግሞ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አይዲኦሎጂ የሚፈቅደውን አምባገነንነት እየደበላለቅን ለመተግበር መሞከር መቆም ይኖርበታል ። ያለው የኢፌዴሪ ህገመንግስት የብዙ መቶ ሺህ ሰማእታት የዘመናት ተጋድሎና ደም ውጤት ነው እያልን በየመድረኩ እያስተጋባን ዞር ብለን ደግሞ ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎችን ከመጣስ አልተቆጠብንም። የኢፌዴሪ ህገመንግስት ለጌጥ ያስቀመጥነው ተራ እቃ አይደለምና ይህ ለምን ይሆናል ነው የወገኖቻችን ተደጋጋሚ ጥያቄዎች እና ውትወታዎች! ይህ አንገብጋቢ ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ ይሻል ያለጥርጥር።

በዴሞክራሲ ግንባታ፣ በሰብአዊ መብቶች አከባበር፣ በተቅዋማት ግንባታ፣ በፓለቲካ ምህዳር ወዘተ ረገድ የእስከዛሬው ጉዞአችን እጅግም አመርቂ አለመሆኑን እኛ ገዥዎች እና የእኛ ደጋፊዎች ለማመን ባንሻም ያለማቋረጥ በሐገር ውስጥና ከሐገር ውጭ አያሌ ወገኖቻችን የሚያሰሙዋቸው ጩሀቶችና እሮሮዎች አይነተኛ ምስክሮች ናቸውና ሊያሳስቡን ይገባል። ባለፉት የአስር አመታት ጊዜ ብቻ እጅግ በርካታ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን በአገሪቱ ቆዳ ስፋት የዘረጋና አለምን ያስደነቀ የባለሁለት አሃዝ (ከ10% እስከ 11%) የኢኮኖሚ እድገት (GDP growth) ያስመዘገበ ፓርቲና አገዛዝ በፓለቲካ ነፃነቶችና መብቶች እጦት ምክንያት ቀስ በቀስ ተሸመድምዶ ሲዳከም ለማየት የሚሻ ዜጋ በፍፁም አይኖርም፣ ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት የሚነገሩትን ህፀፆች አርሞአና አሰተካክሎ ለበለጡ ድሎች እንዲበቃ እንጂ።

ይህ በዚህ እንዳለ ፣ በህገመንግስታችን መሠረት የብሔረሰቦችን ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ በህዝብ ተወካዮችና በፌደሬሽን ምክር ቤት ደረጃዎች እንዲሁም በክልልና በብሔር ደረጃ ለማረጋገጥና ለማዳበር የተደረጉት ገንቢ ጥረቶች ሊካዱ አይቻልም፣ የፖለቲካ ፋይዳቸው አመርቂ ባይሆንም ቢያንስ ቢያንስ ከየብሄረሰቡ አንዳንድ ተወካይ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲሳተፉ ተደርጓልና። ከዚህ በተጨማሪ ፣ በኢህአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች አገዛዝ ክልሎች ስር የሚገኙትን ሕዝቦች ሁሉ ከምንጊዜውም በተሻለ ተቋማዊ ትስስር አንድነታቸውንና ህብረታቸውን እንዲያጠናክሩ የተቀየሰው ሰፊ የህብረት ግንባር (broadbased coalition) እጅግ የሚደነቅ የፓለቲካ ብልህነት ነው፣ የህብረቱ አባል ፓርቲዎች ነጻነትና ስልጣን እኩል ወይም ተመጣጣኝ ቢሆኑ ኖሮ እንዲሁም የክልላዊ ፌዴራላዊ ስርአቱ ተግባራዊነት አጠያያቂ ሆኖ ባይቀር ። ይህቺን የበርካታ ብሄረሰቦች፣ ባህሎችና እምነቶች አገር ባለፉት ዘመናት በጠብመንጃ ሃይልና በፓለቲካ ጋብቻ፣ በጥቅማጥቅሞችና በሃይል እርምጃዎች (carrot

and stick) አንድነትዋን ለማቆየት ሲደረግ የነበረው ውጣ ውረድ የዚህ አይነቱን አስተማማኝ ተቋማዊ ቅርፅ መያዙ ያለውን አገዛዝ የሚያስመሰግነዉ በጎ እርምጃ በሆነ ነበር፣ ቲዎሪውና አተገባበሩ ለየቅል ባይሆኑ ኖሮ።

ከሁሉም በላይ፣ ከሀያ አምስት የአገዛዝ አመታት በሁዋላ የኢፌዴሪ ሕገመንግሥታዊ ሥርአት፣ የህግ የበላይነት፣ የቡድን መብቶችን፣ የግለሰብ ዜጎችን ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማክበርና በማስከበር ረገድ አሁንም ከቀድሞው አፋኝ ስርአቶች እውነታዎች እምብዛም ፈቀቅ እንዳላልን እነዚህ ድምፆች እየጮሁብን ይገኛሉ። ለምን አድሮ ቃሪያ እንሆናለን ነው የጩሀቶቹ መልእክት? ወገኖቻችን በኛ ዘገምተኛ እርምጃዎች ተስፋ ቆርጠው መፍትሄ ፍለጋ ወደውጭ መሪዎችና አገሮች አቤቱታ እንዲያቀርቡ ወይንም የስደትን አማራጭ ለመተግበር እንዲገደዱ ለምን እንገፋፋቸዋለን ነው ጉዳዩ ?

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቢሆንም፣ ሌሎች የበለፀጉና ያደጉ የምእራብም ሆነ የምስራቅ አገሮች እና የአረብም ሆኑ የላቲን አሜሪካ አገሮች በኢኮኖሚ ግንባታ ረገድ ሊያግዙን ይችላሉ ፣ ነገር ግን ወሳኝ የሚሆነው የራሳችን የውስጥ ሐብትና(ሪሶርስ) ጉልበት እንዲሁም በቁርጠኝነትና በህብረት መነሳሳትና የርብርቦሽ ተጋድሎ ብቻ ነው ። ልማትም ሆነ ዴሞክራሲ ከአሜሪካም ሆነ ከኮሪያ፣ ከጃፓንም ሆነ ከታይዋን አይመጣልንም፣ በራሳችን ትግል ብቻ እንጂ። አዎን፣በዚህ መንገድ ነው ዘላቂ ዴሞክራሲም ሆነ ልማት፣ ሰላምም ሆነ የፖለቲካ መረጋጋት ሊያብብና ሊሰፍን የሚችለው። እነዚህን ሁኔታዎች የሰሜን አሜሪካ፣ የአውሮጳ፣ የእስያና ሌሎች ሃያላን አገሮች ሊፈጥሩልን እንደማይችሉና ብንፈልግም እንደማያሳኩልን ያለፉት ዘመናት ታሪክና በግሎባል ደረጃ የተዘረጋው አለምአቀፍ ፍትሃዊ ያልሆነ የፖለቲካ፣የኢኮኖሚ፣ የንግድ፣ የልማት እስትራተጂና ፓሊሲ ፍንትው አድርጎ ያረጋግጥልናል። በተጨማሪም ዴሞክራሲና ልማት፣ ሰላምና የፓለቲካ መረጋጋት በአመፅ፣ በሁከትና በጦርነት መንገዶች ሊመጡ እንደማይችሉና እንዲያውም ከቀድሞ ሁኔታዎች የባሱና የከፉ ቀውሶችን እንዳስከተሉና ሊያስከትሉም እንደሚችሉ (The law of unintended consequences) እኤአ ከ2003 እስካሁን ድረስ በኢራቅ፣ በአፍጋኒስታን፣ በሶሪያ፣ በዩክሬይን የሚካሄዱት የኔቶ ባለቃልኪዳን አገሮች የጣልቃገብነት ጦርነቶች እንዲሁም ከ2010/11 ኣመታት ወዲህ በመጀመሪያ በቱኒዚያ ቀጥሎ ደግሞ በሊቢያ ፣ በግብፅ፣ በሶሪያ፣ ባህሬን-ወዘተ ከውስጥ በመነጩ ብሶቶችና በውጭ ሃይሎች በታገዙና በተቀነባበሩ ማህበራዊ ንቅናቄዎች የተነሳ የተቀጣጠሉት የለውጥ እንቅስቃሴዎች ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው። ከነዚህ እውነታዎች ተገቢውን ትምህርት በመዉሰድ ከማናቸውም የአመፅና የሽብር መንገድ በመራቅ እንዲሁም የማንንም የውጭ ሃይል ጣልቃገብነትና ገንቢ ያልሆነ ተፅእኖ ሳንጋብዝ በራሳችን ቁርጠኛ ውሳኔና በተባበረ የህዝባችን ተጋድሎ እውነተኛና ሌሎቹ የበለፀጉት ሐገሮች ሕዝቦች የሚደሰቱባቸዉን የዴሞክራሲ ፣ የብልፅግና፣ የህግ የበላይነት፣ የሰላም፣ የደህንነት ዋስትና፣ የነፃነት ህይወት ለራሳችንም ሆነ ለህዝቦቻችን ለማስገኘትና ለማጎናፀፍ የምንረባረብበት ወቅት አሁን ነው።

እነዚህን ድሎች ለመቀዳጀት የሐገሪቱ ልሂቃንና ህዝቦች፣ ገዥዎችና ተገዥዎች፣ የፓለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪል ማህበራት፣ አሸናፊዎች እና ተሸናፊዎች ከፍጥጫና ከአክራሪነት በመራቅ ለጋራ ሃገራችን እድገትና ሉአላዊነት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ ስንል እስቲ እንቀራረብ፣ እንመካከር። ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ፣ ግንቦት 17/2007 በተካሄደው ሀገርአቀፍ ምርጫ ህዝባችን ያለማንም ተጽእኖ ድምፁን ሰጥቶ በነፃ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ "100% በ100% ከመረጠን" በሁሃላ ቀድሞውኑ "ሙትቻ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን" (የተከበሩ አቶ አለምነህ መኮንንን አባባል ልጠቀምና) ማሳደድና ማስጮህ ምን አይነት የፖለቲካ ፋይዳ እንደሚያስገኝልን አይገባኝም፣ የማይገባቸውን ታዋቂነትና ጀግንነት እንዲጎናፀፉ ከሚያደርግ በስተቀር። ይህ ለምን ይሆናል፣ በዝረራ ማሸነፋችን ላይ ጥርጣሬ ከሌለን በስተቀር?

ከሁሉም በላይ፣ ህግን አክብረው የተመዘገቡትንና በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱትን የፓለቲካ ፓርቲዎችን ለምን በጠላትነት እንፈርጃቸዋለን? ለምንስ የጥላቻ ፣የመጠፋፋትና የዜሮ ድምር ፓለቲካ እንከተላለን? ከዚህ አይነቱ ቁማር ማን ይሆን የሚያተርፈው? ለምንስ የራሳችንን ወገኖች ወደአመፅና ወደሽብርተኝነት ካምፕ እንዲገቡ እንገፋፋቸዋለን? የጠላቶችን ቁጥር ለመቀነስ መታገል ሲገባን በተቃራኒው እነዚህን ለማብዛት ለምን እንሻለን? ወደሽብርተኝነት የገቡም ካሉ ማናቸውንም የማግባቢያ ዘዴዎች በመጠቀም ወደሰላማዊ የትግል መንገድ እንዲመለሱ ለምን ደግመን ደጋግመን አንሞክርም?

ባለፉት ጥቂት ኣመታት ብቻ ባለሁለት አሃዝ የእኮኖሚ እድገት በማስገኘት የአለም አገሮችን ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፈ ፓርቲና መንግሥት የተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲዎችን በመጨቆን፣ ጋዜጠኞችን በማሰርና በመሳሰሉት አልባሌና ጥቃቅን ህፀፆች የተነሳ መልካም ስሙና ክብሩ ለምን ይበላሻል? እስቲ ቆም ብለን እናሰላስል ስለፕሬስ ነፃነት፣ ጋዜጠኞችና ብሎገሮች 81% አርሶአደር ፣ 19% ብቻ የከተማ ነዋሪ በሆነበትና በኢኮኖሚ እድገት ረገድ እጅግ ሁዋላቀር በሆነ አገራችንና ህብረተሰባችን ውስጥ የሚያሰራጩትን ወሬ/ዜና ማንና ምን ያህል ህዝብ ይሆን የሚያነብበው? ከከተሜው ነዋሪዎች መካከል የተወሰነ ክፍል ካልሆነ በስተቀር! እንግዲህ በዚህ አነስተኛ የፕሬስ ስርጭት መጠን ምናልባት የፕሬሱ ውጤት አሉታዊና አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ያዘለ እንኳዋን ቢሆን በዚህ የተነሳ መንግሥትንና ህዝብን የሚያሰጋ መሬት አንቀጥቅጥ ማህበራዊ አብዮት ሊነሳ ይችላል ብለን እንሰጋለን ወይ? በኔ እምነት በጭራሽ! ታዲያ በህገመንግስታችንና እርሱን በማይጣረሱ አዋጆች/ሕጎች መሰረት የተደነገጉትን ገደቦች እስካልጣሱ ድረስ ጋዜጠኞችና ብሎገሮች የፈለጉትን ሁሉ በነፃነት እንዲጽፉ መፈቀድ የለበትምን? ህግን ያልተቃረነ ሃሳብን በነፃነት መግለጽ ለምን የነብርን ጅራት እንደመንካት አስፈሪና አስጊ ሆኖ ይቆጠራል? ኢህአዴግ በ1983 ባወጣው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሙ ላይ (ገፅ 6) እንዲሁም በ1994 ባፀደቀዉ የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 27፣ 29፣ 30፣ እና 31ላይ በግልጽ የደነገጋቸውን የሃይማኖት ፣የእምነትና የአመለካከት ነፃነት ፣የአመለካከት፣ ሐሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት፣ የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት እና የመደራጀት መብት በግላጭ ይጥሳል የሚሉ ስሞታዎች ለምን ይሰማሉ? እነዚያን ለኢህአዴግ ፕሮግራም ተግባራዊነት እና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሲታገሉ በየከተሞቹና በየገጠሮቹ ፣ በየተራሮቹና በየዱር ገደሉ፣በየበረሃውና በየሸንተረሩ የወደቁትን ጀግኖች ሰማእታት ዛሬ በነርሱ የደምና የሕይወት መስዋእትነት መንግስታዊ ስልጣን የያዘው ድርጅት ራሱ ያፀደቃቸውን ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎችን ይጥሳል ብለን እንዴት በድፍረት እንኮንነው? እነዚህ ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎች በገዥው መንግስት ባለሥልጣናት በማንአለብኝነት ከተጨፈለቁ የፕሬስ ነፃነትስ እንዴት ሊኖር ይችላል? የፕሬስ ነፃነት ማበብ እኮ ገዥው ፓርቲ እና

መንግሥት ጉድለቶቻቸውን በወቅቱ እንዲያርሙ አይነተኛ ሚና እንደሚጫወት እንዴት ተዘነጋ? የሰላማዊ/ህጋዊ ተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲዎች መኖርና መጠናከርም ተመሳሳይ ገንቢ ሚና እንዳለዉ መዘንጋት የለበትም እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት በመገንባት ረገድ የጠራ አቅዋም የምናራምድ ከሆነ። በዚህም መሠረት በህገመንግስታዊ ስርኣት መጎልበት ረገድ ግልፅና የማያወላዳ አቅዋም እንድናራምድ የግድ ይላል። በሆነው ባልሆነው ሁሉ ሰዎችን ሕገመንግሥታችንና እርሱን ተመርኩዘው የወጡ ሕጎች ከሚፈቅዱት ውጭ ማሰር ዜጎችን መበደልና ህገመንግስታችንን መጣስ ከመሆኑም በላይ በመንግስታችን ላይ ከፍተኛ ወጭ እንደሚያስከትል መታወቅ ይኖርበታል። አንዳንዴም እኮ አንዳንድ መናኛ ጥፋቶችን በተመለከተ እያዩ እንዳላዩ፣ እየሰሙም እንዳልሰሙ ሆነው ወይንም ስቆ ማሳለፍ እኮ የበሳል መሪዎችና ሰዎች የሚደነቅ ችሎታ ነው፣ ጥበብ ነው። በመጨረሻም፣ ለራሳችን፣ለልጆቻችንና ለቤተሰቦቻችን የሰላም ኑሮ እንዲኖሩ እንደምንመኝ ሁሉ ለሌሎች ዜጎችም ሰላማዊ ኑሮ ስንል የነርሱንም መብቶች በሚገባ እናክብር፣ እናስከብር። የሰላምን አማራጭ ከሁሉም አማራጮች ሁሉ እናስቀድም።

ከዚህ በላይ የተገለጸውን የሪፓርተር ጋዜጣን ትችት በተመለከተ፣ ህዝብ ዴሞክራሲ እንዲሰፍንለት ከመንግሥት የሚጠብቅበትን ጊዜ ማሳጠርም ሆነ ማዘግየት የሚችለው ህዝቡ ራሱ ነው፣ ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ ስርአተ መንግሥት ስር ለመኖር አንፈቅድም የሚል ብርቱ አቅም ሲያገኝ ወይም ሲያጣ ነው። አቅሙን ያዳበረ እለት ግን በእጁ ያለውን የምርጫ ካርድ በምርጫ ሳጥን ውስጥ በመክተት ድጋፉን በመስጠት ወይም በመንፈግ ይወስናል፣ በሥልጣን ያለውን አገዛዝ ያወርዳል ወይም ተጨማሪ የአገልግሎት ጊዜ በኮንትራት መልክ ይሰጠዋል ወይንም ደግሞ ሌላ አገዛዝ ያስቀምጣል። በተለያዩ ምክንያቶች ይህን አቅምና ጉልበት ያጣ ህዝብ ግን ዴሞክራሲን ከገዥዎቹ ሲጠብቅ ይኖራል፣ ወይንም ጫናውን መሸከም ሲያቅተዉ ያምፃል፣ሌላ ምን አማራጭ አለው? ከሁሉም በላይ፣ አንድ ህዝብ ዴሞክራሲን አገዛዙ እንዲያሰፍንለት መጠበቅ ሳይሆን ማስገደድ ነው ያለበት። ይህንን ማድረግ ካልቻለ ለዝንተኣለም በፍርሃት መገዛት ነው እጣ ፈንታው።;

በመጨረሻም፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ዛሬ የምንገኝበት ወቅት እጅግ አስፈሪ የሆኑ የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ አደጋዎች ያንዣበቡብን ወቅት ነው ብል ማጋነን አይመስለኝም። በመጀመሪያ፣ ባለፉት ሰላሳ አመታት ደርሶ በማያውቅ ክስተት ከ10—15 ሚሊዮን የሚበልጡ ወገኖቻችን ለችጋር የተጋለጡበት አሰቃቂ ጊዜ ነው። ይህንን ብሔራዊ አደጋ ለመቋቋቋም የሚያስፈልገውን የህዝብ አንድነት፣ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ምንጭ እንዲሁም ብሔራዊ ንቅናቄ የሚፈታተኑ ሁኔታዎች የበላይነትን ተቀዳጅተው አገራችንን ለከፉ አደጋዎች እንዳያጋልጡን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የዜጎች ሁሉ የውዴታ ግዴታ ነው። በሁለተኛ ደረጃ፣ አክራሪ ፖለቲከኞችን እና የሙስሊም አክራሪዎችን ከኤርትራ መንግሥት ጋር ተመሳጥረው በገንዘብና በመሳሪያ ሃይል በማስታጠቅ አገራችንን ወደብጥብጥና ወደመበታተን እንዲሁም ከተቻለም ወደኢስላሚክ እስቴት ለመለወጥ እያሴሩ ያሉ እንደሳኡዲ አረቢያ፣ ግብፅ እና ኳታር በሙሉ ሃይል እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ የሚያስጠነቅቁ መረጃዎች ከተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች እየጎረፉልን ስለሆነ እነዚህ ተራ ዘገባዎች ወይንም መሰረተቢስ የconspiracy መላምቶች ናቸው ብለን መዘናጋት አይኖርብንም።

ከሁሉም በላይ መገንዘብ ያለብን ቁምነገር ፣ ጊዜ ሲፈቅድ አገዛዝ ይነሳል፣ ጊዜ ሲከዳው ወይንም ህዝብ ከጠላዉና ድምፅ ከነፈገዉ ደግሞ ይለወጣል ወይም ይወድቃል፣ የሃይል ሚዛን ተለዋዋጭ ነው፣ ትናንት ወዲያና ትናንትና እንደነበሩት አገዛዞች ሁሉ። የጊዜ እንጂ የሰው ጀግና የለውም እንደተባለው። የመሪዎች ሕይወትም የተወሰነ ነው፣ ሞት የሚሉትን እዳ ከመክፈል የሚተርፍ የለምና። የፓለቲካ ሥልጣን ለሀብት ቁጥጥርና ዝርፊያ አይነተኛ መሣሪያ መሆኑ ባይካድም ይዋል ይደር ያከማቹት ሀብትም እኮ ያልቃል። የፓለቲካ ስልጣንም ጊዜያዊ ነው፣ መውጣት እንዳለ መውረድም አይቀሬ ነው፣ ጊዜው ቢረዝምም ቢያጥርም። በሰፈሩት ቁና መሰፈርም የማይቀር እዳ ነዉ፣ የዘሩትን ማጨድ፣ ክፉም ሆነ ደግ። የነገውንና የመጪውን ጊዜ አርቆና አሻቅቦ መተንበይ ለሁላችንም ይበጃል እንጂ ጉዳት አያስከትልም። "ሶጤካ ላኦቤ ሃዮኢ፣ ሻ ግቦቤ ቆጠሪ" የሚለውን የሐዲያ ብእል ልብ ይሉዋል! (ትርጉሙም፣ ገድሎ የማይሸሽ ጀግና እና የነገውን አርቆ ለማስተዋል/ለመተንበይ የማይችል አዋቂ አንድ ናቸው፣ ማለት ነው)። ሁልጊዜም ለሚኖረው አገራችንና ለማያልፈው ህዝባችን የማያልፍ ዘላቂ የዴሞክራሲ እና የልማት ገንቢ ታሪክ ሰርተን ለማለፍ በቁርጠኝነት እንነሳ። የጋራ አገራችንና ዞሮ መግቢያችን፣ የጋራ ቤታችንና መከበሪያችን/መቀበሪያችን እንዳትዳከምና እንዳትፈራርስ ብርቱ ጥንቃቄዎችን የምናደርግበት ዘመን ላይ እንደምንገኝ ሁላችንም አንዘናጋ እላለሁ። ጆን ኤፍ ኬኔዲ እንዳለው፣ "ሰላማዊ አብዮትን የሚከላከሉ ሁሉ አመፅ የተሞላበትን አብዮት አይቀሬ ያደርጉታልና" የአገራችን እጣ ፈንታ በሠላማዊ መንገድ የሚመጣ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት እንዲሆን የፖለቲካ ልሂቃንና መላው ሕዝባችን በቁርጠኝነት እንዲታገሉ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።ሌላው አማራጭ ሁሉ የመጠፋፋትና የመበተታን ጎዳና ነውና።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።